# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

# የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት እና ብቃትን ለማረጋገጥ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ

የአገራችንን የሎጂስቲክስ ዘርፍ አፈጻጸም ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎትን ለግል ባለሃብት ክፍት እንዲሆን በማድረግ ጠንካራና ተወዳዳሪ አገልግሎት ሰጪ እንዲፈጠር ማድረግ እንዲሁም ዘርፉ በውድድር እንዲመራ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአገራችን ዓለም አቀፍ የገቢ እና የወጪ ንግድ ዕቃ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ በዓይነትም ሆነ በመጠን እየሰፋ መጥቷል፤ እያደገ የመጣውን የአገራችንን የዓለም አቀፍ ንግድ ዕቃ በአንድ ብቸኛ የሞልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አገልግሎቱን በበቂ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ እንደማይቻል በመታመኑ፣

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር ማሳደግ አገራችን በዓለም አቀፍ የገቢ እና ወጪ ንግድ ለትራንስፖርት፣ ለባሕር ወደብ ቆይታ፣ ለመጋዘን ቆይታ በውጭ ምንዛሪ የምታወጣውን ወጪ በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በመታመኑ፤

በመንግስት የልማት ድርጅት የተያዘውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ለግል ባላሃብቱ ክፍት በማድረግ አገልግሎቱ በውድድር እንዲመሰረት በማስቻል የተገልጋዩንና የህዝብን ተጠቃሚነት ብሎም የአገልግሎት ጥራትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980 አንቀጽ 21 (4) (በ) እና የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) ላይ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት አከናዋኝ የንግድ ፍቃድ ለመስጠት እና ብቃት የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ይህን መመሪያ አውጥቷል፤

DRAFT

# <u>ክፍል አንድ</u>

# <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ሥራ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር ------/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

በአዋጁ የተሰጠ የቃል ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. **"አዋጅ"** ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 ነው፤
2. "ዕቃ ተረካቢ"፣ "ዕቃ ላኪ"፣ "ርክክብ"፣ "ዓለም አቀፍ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት"፣ "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ" "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ"፣ "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል"፣ "የትራንስፖርት አይነት"፣ "ዕቃ" ፣ "ኃላፊነት መውሰድ"፣ "ማስረከብ"፣ የሚሉት ቃላትና ሐረጎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 የተሠጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤
3. **"ባለሥልጣን"** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤
4. **"ድርጅት"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፤
5. **"ኩባንያ"** ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር፣ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣
6. **"በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት"** ማለት ኢትዮጵያዊ ወይም አግባብ ባለው ህግ እንደ አገር ውስጥ ባለሃብት የተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ እና የውጭ ካፒታል ወደ አገር ውስጥ ይዞ የገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም እንደ ውጭ ባለሃብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ጋር በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው፡፡

DRAFT

7. **"የሥራ ፈቃድ"** ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በዚህ መመሪያ ሥር ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት በባለሥልጣኑ የተሠጠ የፀና የሥራ ፈቃድ ነው፤

8. **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

9. **"ብሔራዊ ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

10. **"አንድ ወጥ የሆነ ታሪፍ"** ማለት የመልቲሞዳል አከናዋኙ ከዕቃ መነሻ ወይም ዕቃውን ከተረከበበት ቦታ እስከ ማስረከቢያ የሀገር ውስጥ መዳረሻ ድረስ ያለውን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ወጪ ለደንበኛው የሚያሳውቅበት የተጠቃለለ የአገልግሎት ዋጋ ነው፡፡

11. **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በዚህ መመሪያ በተወሰነው ዝርዝር መስፈርት መሰረት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል ብቃት መኖሩ ሲረጋገጥ ይህንኑ ስራ ለመስራት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

12. **"ወኪል"** ማለት ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ የመልቲ ሞዳልትራንስፖርት አገልግሎት የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ውክልና የተሰጠው በሙያው በተወከለበት ሀገር የተመዘገበና የስራ ፍቃድ ያለው ድርጅት ወይም ኩባንያ ነው፡፡

13. **"ማስረከቢያ ቦታ"** ማለት በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ ገቢ ጭነቶች መዳረሻ እንዲሆን የተወሰነ ቦታ ማለት ነው፡፡

14. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

## 3· <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በማንኛውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ እና የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሠነድ በተሠጠባቸው ማናቸውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4· <u>የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተግባራት</u>

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚያከናውናቸው ሥራዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

1. ከዕቃ አስመጭው/ላኪው ጋር በሚያደርገው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ቢያንስ ሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶችን በመጠቀም ዕቃን ከአንድ የተወሰነ በውጭ ሀገራት በሚገኝ መነሻ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሀገር ውስጥ በሚገኝ ማስረከቢያ ቦታ ወይም ለዕቃ ተረካቢ ማስረከብ፤
2. ዕቃዎችን የማቀናጀት፣ ዕቃዎችን ለያይቶ የማስረከብ፣ የዕቃዎች ማከማቻ/ማቆያ አገልግሎት፣ የዕቃ ማስተናገጃ መሣሪያ አገልግሎት፣ የተርሚናል እና የኮንቴይነር ማስተናገድ አገልግሎት መስጠት፤
3. በአዋጁ መሠረት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ማዘጋጀት፣ ለዕቃ ላኪው መስጠት፣
4. ባለሥልጣኑ በሚያጸድቀው አንድ ወጥ በሆነ ታሪፍ የመልቲሞዳል ትራስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
5. በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለሚያጓጉዘው ዕቃ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለባለዕቃው፣ ለባለሥልጣኑ፣ ለመዳረሻ ጣቢያው መስጠት እና የጭነቱን ፍሰት መከታተል እና መቆጣጠር፣
6. በሀገር ውስጥ የጉምሩክ ስርዓት በሚፈጸምባቸው ቦታዎች ወይም በመንግስት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት መዳረሻ ሆነው በተሰየሙ ማናቸውም ቦታዎች ብቻ ዕቃዎችን ለደንበኛው ማስረከብ ወይም እንዲቆዩ ማድረግ፣
7. የተረከበውን ዕቃ ደህንነት በመጠበቅ ከመነሻ ቦታ ከዕቃ ላኪው ወይም ወኪሉ በተረከበበት ሁኔታ ለተረካቢው ማስረከብ፤
8. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጭነቱ የመጨረሻ መድረሻ ቦታ በመጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል በጉምሩክ ኮሚሽን የሚጠየቅ የጉምሩክ ዋስትና ማቅረብ፣
9. ህጋዊ ዕውቅና ባለው የውጭ ኦዲተር ሊመረመር የሚችልና የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 847/2006 የተከተለ የሂሳብ መዝገብ ሥራ ላይ ማዋል፣ ናቸው፡፡

DRAFT

# ክፍል ሁለት

# የሥራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ

## 5. የሥራ ፈቃድ ስለማስፈለጉ፣

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለሥልጣኑ የሥራ ፈቃድ ሣያገኝ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት ሥራን (መሥራት) መጀመር ወይም መቀጠል አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለሥልጣኑ የሥራ ፈቃድ ሣያገኝ “የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ” የሚል ኃረግ የተጨመረበትን የንግድ ስም መጠቀም አይችልም፡፡

## 6. መሰረታዊ ብቁነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር፣ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ በኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች ወይም በኢትዮጵያውያንና በውጭ ባለሃብቶች በቅንጅት ኢንቨስትመንት የተቋቋመ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የንግድ ሥራ መስክ ለመሠማራት በሕግ መብት የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ሚኒስቴሩ ለወደፊት የአከናዋኞቹን አፅንታዊ ውጤት እያየ ቁጥራቸውን ሊጨምር የሚችልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ባላቸው አደረጃጀትና የካፒታል መጠን በቀዳሚነት የሚመረጡ ከአምስት ያልበለጡ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ይሆናሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በመልቲሞዳል ትራስፖርት አከናዋኝነት የሚሰማሩ ኩባንያዎችን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ በተመለከቱት እና ባለሥልጣኑ ወደፊት በሚያወጣው የማወዳደሪያ መስፈርት መሠረት በሚካሄድ ግልፅ ውድድር ተመርጠው የሚሠየሙ ይሆናል፡፡

DRAFT

## 7· የሥራ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል መስፈርት፣

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ በአመልካቹ በሚገባ የተሞላ የሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነውን የአገልግሎት ክፍያ እና ባለሥልጣኑ ከሚጠይቃቸዉ ሌሎች በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 አና 7 ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 5 የተመለከቱትን አባሪ ማሥረጃዎች ጋር አብሮ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የመልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን በአግባቡ ለማካሄድ እና የንግድ እንቅስቃሴውን ለመምራት የሚያስችል ጠንካራ አመራርና አደረጃጀት እንዲሁም በቂ የፋይናንስ አቅም ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

    ሀ. የኩባንያው ወይም የቅንጅት ኢንቨስትመንት መመስረቻ ፅሁፍ፣ የመተዳዳሪያ ደንብ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ መቅረቡን፣

    ለ. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ዝግጅት ኖሯቸው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቢያንስ በአንዱ (በጭነት ማስተላለፍ፣ በመርከብ ውክልና፣ በሺፒንግ ኦፐሬሽን፣ በወደብ ኦፐሬሽን፣ በጭነት ትራንስፖርት፣ በባንክና ኢንሹራንስ፤ ዓለም አቀፍ የማሪታይም ህግ፤ በትራንዚትና የጉምሩክ መብት ማስፈፀም ሥራዎች) ሥራ አመራርና ኦፐሬሽን እንዲሁም ጥናትና ምርምር ከ5 ዓመት ያላነሰ የሥራ ልምድ ባላቸው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚመራ መሆኑ፤

    ሐ. ኩባንያው/ድርጅቱ በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ብር 350 ሚሊዮን (ሶስት መቶ ሃማሳ ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 10 በመቶው በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ የተቀመጠ ቀሪው 90 በመቶ ደግሞ በተለያዩ ንብረቶች ማለትም በትራንስፖርት መሳሪያዎች፣ በዕቃ ማስተናገጃ መሳሪያዎች፣ በመጋዘኖች፣ በቢሮ ህንጻዎች፣…ወዘተ መልክ ያለው መሆኑን፣

    መ. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል መሠረት ከዕቃ ላኪው ተረክቦ የሚያጓጉዘው ዕቃ ቢጠፋ ወይም ቢጎዳ ወይም ቢዘገይ ወይም ከውል የመነጨ ሌሎች የኃላፊነት ሁኔታዎች ቢኖሩበት አስፈላጊውን ካሣ ለመክፈል የሚያበቃ የመድን ዋስትና

DRAFT

ከመድን ሰጪ ኩባንያ በራሱ ወይም በሌላ ውል በቀጠራቸው ድርጅቶች በኩል ያለው መሆኑን፣

ሠ. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጭነቱ የመጨረሻ መድረሻ ቦታ በመጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል የጉምሩክ ኮሚሽን በሚወስነው የአከፋፈል ዓይነትና የገንዘብ መጠን ልክ የቀረጥና ታክስ ዋስትና ለማቅረብ የተሠጠ መተማመኛ መኖሩን፣

ረ. ኩባንያው ወይም አንድና ከዚያ በላይ የሆኑት ባለድርሻዎቹ እንደ ድርጅት በጭነት ማስተላለፍ፣ በመርከብ ውክልና፣ በባህር ማጓጓዝ፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ኦፕሬተርነት፣ በአየር ትራንስፖርት፣ በድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት፣ በወደብ ማስተዳደር ወይም ከነዚህ በአንዱ የሥራ መስክ ቢያንስ የ5 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው መሆኑን፣

3. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የሚከተሉትን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ማሟላቱን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት።

ሀ. ለሚያከናውነው ሥራ በሥራው መጠንና በሠራተኞቹ ልክ የሚያስፈልጉ በቂ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ መኖሩን፣

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7፣ ን/አንቀጽ 2 (ለ) ላይ የተመለከተውን መስፈርት በሚያሟሉ እንዲሁም ቁጥራቸው ከ7 ባላነስና ከ12 ባልበለጠ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመራ መሆኑን፣

ሐ. የተሟላ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲሁም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥራን ለመምራት የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ ሠልጥነው በጭነት አስተላላፊነት፣ በትራንዚተርነት፣ በወደብ ሥራ አመራር ወይም ኦፕሬሽን፣ በድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት ሥራአመራር ወይም ኦፕሬሽን፣ በመርከብ ውክልና፤ ዓለም አቀፍ የማሪታይም ህግ ወይም በሌሎች ዓለም አቀፍ የንግድ ሎጀስቲክስ አሠራሮች ቢያንስ የ8 ዓመታት የሥራ ልምድ ያላቸው ከ15 ያላነሱ የሠለጠኑ ሠራተኞች እና ከነዚህ መካከል ቢያንስ 5ቱ የኩባንያው/የድርጅቱን ከፍተኛ የሥራ መሪ ጨምሮ መሰረታዊ የሆኑትን ከፍተኛ የኦፕሬሽን ሥራ የሚመሩ ብቁ የሥራ መሪዎች ያሉት መሆኑን፣

DRAFT

መ. በቦርዱ የፀደቀ የተሟላ የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅር (በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚመራና በሥሩ ራሳቸውን የቻሉ ቢያንስ የኦፐሬሽን (በሺፒንግ፣ በፎርወርዲንግ፣ በየብስና በአየር ትራንስፖርት፣ በወደብ የሥራ ዘርፎች)፣ የፋይናንስ እና ሊሎች አስፈላጊ ድጋፍ ሰጪ የስራ ክፍሎች ያሉት ሆኖ የእንያዳንዱ የድርጅቱ ሠራተኞች የቅጥር ውል፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሁም ቦርዱ የጸደቀ የሥራ ሃላፊዎችን የተሰየሙበት ማስረጃ መኖሩን፣

ሠ. ባግባቡ የታጠረና ደህንነቱ የተጠበቀ በትንሹ 5 ሄክታር ቦታ በባለቤትነት ወይም ከ4 ዓመት ያላነስ ጊዜ ኪራይ ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 3 ሄክታር የለማ ተርሚናል እና ከ3,000 ካ/ሜ ያላነሰ ስፋት ያለው በኮንክሪትና በብሎኬት የተሰራ ዝግ መጋዘን ያለው መሆኑን፣

ረ. አንድ ሪችስታከር ወይም ክሬን በባለቤትነት ወይም ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ፣ በአንድ ጊዜ ቢያንስ 380 ኩ/ል ማንሳት የሚችሉ 30 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነትና ሌሎች ተጨማሪ 40 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በኪራይ፣ቢያንስ አንድ ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው እና ሁለት ፎርክሊፍት በባለቤትነት ማቅረብ የሚችል፤

ሰ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥባቸው የውጭ ሀገራት እና ወደቦች (ከነዚህ አንዱ ጅቡቲ የሆነ) ኩባንያው/ድርጅቱ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ወኪል ያለው ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ከየሃገራቱ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣን ማቅረብ የሚችል እና 3 የሃገር ውስጥ ቅርንጫፎች ያሉት መሆኑን፣

ሸ. የኢትዮጵያ ገቢ ዕቃ መዳረሻ በሆኑ የውጭ ሀገራት የባህር ወደቦች (ከነዚህ አንዱ ጅቡቲ የሆነ) የትራንዚት ሥራውን የሚያስተባብርለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 (3) (ሐ) ላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት የትምህርት ዘርፎች ውስጥ በአንዱ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከአምስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያለው ቢያንስ አንድ ቅጥር ሠራተኞች ያለው ማስተባበሪያ ቢሮ፤

ቀ. እንደመልቲሞዳል አከናዋኝ ሃላፊነት ወስዶ ለሚያጓጉዛቸው ዕቃዎች የባህርና የየብስ ኢንሹራንስ ሽፋን ማቅረብ ወይም በመልቲሞዳል ሥርዓት ለማጓጓዝ ሃላፊነት የወሰደባቸውን ዕቃዎች በባህር ወይም በየብስ እንዲያጓጉዙ በውል



DRAFT

የሚቀጥራቸው አንጓዦች በዓለም ዓቀፍ የባህር ትራንስፖርት የዋስትና አሠጣጥ ስርዓት (P&I Club) ወይም በየሚተላለፉባቸው ሃገሮች የየብስ ትራንስፖርት ህግ መሰረት ለሚያጓጉዙት ጭነት ሙሉ ዋስትና (Carriers Liability Insurance) ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል፤ሆኖም ግን በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 15 መሰረት ሙሉ ሃላፊነቱን መልቲሞዳል አከናዋኙ ይወስዳል፡፡

በ. ከሃገር ውስጥም ሆነ ውጭ ወኪሎቹ ዕቃን በባህርና በየብስ ከሚያጓጉዙ ኩባንያዎች፣ ከዓለም ዓቀፍ የባህርና የሃገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች፣ ከኢትዮያጽና ጅቡቲ ጉምሩክ እንዲሁም ሌሎች ዋና ዋና የዘርፉ ባለድርሻዎች ጋር በቀላሉ መረጃና ትዕዛዝ ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥራውን የሚመጥን ደረጃውን የጠበቀ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማትና የመገናኛ ዘዴ ያለው፤

ተ. በሃገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ አካውንት ያለው ወይም መክፈት የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብ፤

ቸ. በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 (4) መሰረት የተዘጋጀ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሠነድ ማዘጋጀት፣ማተምና መሥጠት የሚችል፤

4. የሚቋቋመው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ዋና መሥሪያ ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፣

## 8. <u>የሥራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት ማመልከቻና አብረው መቅረብ ያለባቸዉ ማስረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡለት በመጀመሪያ አመልካቹ ባቀረበው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የብቃት ማረጋገጫ ቀጥሎ ቋሚ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም አመልካቹ በአንቀጽ 6 እና 7 ላይ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች ባንድ ጊዜ ማሟላት ካልቻለ የተወሰኑትን መስፈርቶች ብቻ እንዲያላሟና ጊዜያዊ ፈቃድ ተሰጥቶት አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ሊጠይቅና በባለስልጣኑ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ ይሁንና አመልካቹ ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሠጠው የሚችለው የሚከተሉትን ዝቅተኛ መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ እነዚህም፡-

DRAFT

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ላይ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች፤

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7፤ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ፣ለ፣መ፤ሠ እና ረ)፣ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ፣ ለ፤ ሐ፤ መ፤ ሰ፤ ሸ፤ ቀ፤ በ፤ ተ እና ቸ)፤ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች፤

ሐ.በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ብር 228 ሚሊዮን (ሶስት መቶ ሃማሳ ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 10 በመቶው በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ የተቀመጠ ቀሪው 90 በመቶ ደግሞ በተለያዩ ንብረቶች ማለትም በትራንስፖርት መሳሪያዎች፣ በዕቃ ማስተናገጃ መሳሪያዎች፣ በመጋዘኖች፣ በቢሮ ህንጻዎች፣...ወዘተ መልክ፤

ረ. ባግባቡ የታጠረና ደህንነቱ የተጠበቀ በትንሹ 3.5 ሄክታር ቦታ በባለቤትነት ወይም ከ4 ዓመት ያላነስ ጊዜ ኪራይ ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 2 ሄክታር የለማ ተርሚናል እና ከ2,000 ካ/ሜ ያላነሰ ስፋት ያለው በኮንክሪትና በብሎኬት የተሰራ ዝግ መጋዘን፤

ሰ. አንድ ሪችስታከር ወይም ክሬን በባለቤትነት ወይም ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ፣ በአንድ ጊዜ ቢያንስ 380 ኩ/ል ማንሳት የሚችሉ 20 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነትና ሌሎች ተጨማሪ 30 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በኪራይ እንዲሁም ቢያንስ አንድ ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው እና በአመልካቹ ባለቤትነት ተመዘገበ አንድ ፎርክሊፍት፤ ይሆናሉ፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ን/አንቀፅ 2 የተመለከተው ቢኖርም የጊዜያዊ ፈቃዱ የአገልግሎት ዘመን በማናቸውም ሁኔታ ከ1 ዓመት አይበልጥም፤
4. ጊዜያዊ ፈቃድ የተሰጠው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዝርዝር ባለስልጣኑ በሚያወጣው የአሰራር ስርዓት ተለይቶ ይቀርባል፤
5. የሥራ ፈቃዱ የሚሰጠው በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነውን የሥራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ አመልካቹ ለባለሥልጣኑ ሲከፍል ይሆናል፡፡
6. በዚህ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ የተስጠ የሥራ ፈቃድ እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የመልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻ የብቃት ማረጋገጫ እና የሥራ ፍቃድ ይሆናል፡፡

DRAFT

# ክፍል ሦስት

# የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ግዴታዎችና ክልከላ

## 9. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ግዴታዎች

በአዋጁ ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ግዴታዎች የሚከተሉትን ያካትታል፣

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃ በሚያንገዝባቸው የውጪ አገሮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ወኪል ሊኖረው ይገባል፣
2. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ወይም ወኪሎችን ስምና አድራሻ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሥራ ከመጀመሩ 15 ቀናት አስቀድሞ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ አቅርቦ ማስመዝገብ፣
3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለሚሰጠው አገልግሎት ሥራ ላይ የሚያውለውን ታሪፍ ስራ ከመጀመሩ/ከመቀጠሉ አንድ ወር አስቀድሞ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ያቀርባል፤
4. በባለሥልጣኑ የጸደቀ ታሪፍ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ቢያንስ ለ6 ወራት ሥራ ላይ ማቆየት ይኖርበታል፣ ሆኖም ግን አስገዳጅ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ አከናዋኙ በማንኛውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ታሪፉ እንዲከለስ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፣
5. የዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 3 ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ን/አንቀጽ 7 እና 8 ላይ እንደ ተገለጸው ባለሥልጣኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ታሪፉ ስለመጽደቁ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ምላሽ ያልሰጠ ከሆነ በመልቲሞዳል አከናዋኙ የተዘጋጀው ረቂቅ ታሪፍ በባለሥልጣኑ እንደጸደቀ ተቆጥሮ ሥራ ላይ ይውላል፣
6. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ የተዘረዘሩትን እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ዝርዝሮች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣
   ሀ) የሰነድ መለያ ቁጥር፣
   ለ) የዕቃ ላኪው ስም፣
   ሐ) በላኪው የተጠቀሰ ከሆነ የተረካቢው ስም፣
   መ) የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ስምና መደበኛ የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታው፣
   ሠ) መልቲሞዳል የትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን የተረከበበት ቀንና ቦታ፣
   ረ) ዕቃውን የጫነው የመርከብ/የአይሮፕላን ስምና የጉዞ ቁጥር፣

DRAFT

ሰ) ዕቃውን አጓጉዞ የማስረከቢያ ቦታ፣

ሸ) የዕቃው ውጫዊ ሁኔታ መግለጫ፣

ቀ) በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረገበት ከሆነ የማስረከቢያ ቦታ፤

በ) የዕቃው አጠቃላይ ሁኔታ፤ ዕቃውን ለመለየት አስፈላጊ የሆኑ መሪ ምልክቶች፤ ዕቃው አደገኛ ከሆነ አደገኛነቱን የሚገልጹ ጽሁፎችን፤ የዕሽጎቹን ወይም የነጠላ ዕቃውን ቁጥርና የዕቃውን አጠቃላይ ክብደት ወይም በመጠን የተገለጸ ከሆነ ይህንኑ በዕቃ ላኪ የሚሰጡ ዝርዝሮችን፤

የሚገልጽ መሆን አለበት፣

7. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ አደገኛ የሆኑ ጭነቶችን በሚያጓጉዝበት ወቅት ከዕቃ ላኪው የአደገኛ ጭነት መግለጫ ሰነዶችን መረከብና ለሚመለከታቸው (ወደብ፣ የየብስ አጓጓዥና ሌሎች) በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፣
8. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን እንደተረከበ የሚጠቀምበትን ሰነድ በማዘጋጀት ለዕቃ ላኪው ወይም ተቀባዩ በሃርድ ኮፒ ወይም ስካን በተደረገ ሶፍት ኮፒ ወይም ኦንላይ በተዘጋጀ ፕሪንት አውት በግንባር፤ በፓስታ ወይም በኢሜይል ወይም በሌላ ማናቸውም ዓለማቀፍ ተቀባይነት ባለው የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴ መስጠት አለበት፤
9. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የተረከበውን ዕቃ በተመለከተ ባለዕቃው ስለ ዕቃው መረጃ ማወቅ በፈለገበት በማንኛውም ጊዜ ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴን በመጠቀም ለባለዕቃው በሚሰጥ ሚስጥር ቁጥር አማካኝነት እንዲከታተል ማመቻቸት አለበት፤
10. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን አጓጉዞ በመልቲሞዳል ሰነዱ በተገለጸው የመጨረሻ መዳረሻ ቦታ ከመድረሱ በፊት በጭነት መኪና ከሆነ 48 ሰዓት በባቡር ከሆነ 12 ሰዓት አስቀድሞ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ወይም በፋክስ ወይም በስልክ ቴክስት ወይም በሌላ በማናቸውም ዓለም አቀፍ መገናኛ ዘዴ በአድራሻ ለባለዕቃው እና በግልባጭ ዕቃው ማራገፊያ ቦታ ላይ ለሚገኝ የደረቅ ወደብ ወይም ተርሚናል ኦፕሬተር ማሳወቅ አለበት፤
11. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለባለዕቃው የተላኩ መልዕክቶችን እንዲሁም ከማናቸውም ጋር የተደረጉ የፋይናንስ ልውውጦች፣ የሥራ ግንኙነቶችንና ከሥራው ጋር የተያያዙ የተሟሉ መረጃና ሰነዶችን ማደራጀት ሪኮርዶችን መመዝገብ እና እስከ አምስት

DRAFT

አመት ድረስ ይዞ ማቆየት እንደ አስፈላጊነቱም ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸውን ሰነዶችና መረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤

12. በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ ከተቀመጠ 10 በመቶ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ በዝግ አካውንት ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

13. በዝግ አካውንት የሚቀመጠው ገንዘብ ቢያንስ ለ3 ወር ሆኖ ባለሥልጣኑ ለመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሥራ ፈቃድ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ከ3 ወራት በኂላ በ5 ቀናት ውስጥ የሚለቀቅ ይሆናል፤

14. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሀገሪቱን የውጭ ንግድ ደንቦችን፣ በሌላ መመሪያ የተወሰነውን የዓለም አቀፍ የግብይት ዘዴን (ኢንኮተርምን) ግዴታና አቅጣጫ ተግባር ላይ ማዋል አለበት፣

15. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለማጓጓዝ በሃላፊነት የተረከበውን ዕቃ ደህንነት መጠበቅ አለበት፤ ዕቃው በቁጥጥሩ ሥር እያለ ወይም በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ወይም በወኪሉ ወይም በሰራተኞቹ ጥፋት/ስህተት ቢጠፋ፣ ቢበላሽ፣ ቢዘገይ፣ ቢጎዳ ወይም ቢባክን ኃላፊነቱን ይወሰዳል፣

## 10· <u>ክልከላ</u>

1. ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ካላገኘ በስተቀር ማንኛውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚከተሉትን መፈጸም አይፈቀድለትም፣

   ሀ. በሀገር ውስጥ ከሚገኝ ከሌላ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ጋር መቀላቀል፤ ማንኛውም አይነት ሽርክና መፈጸም ወይም ሌላውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተክቶ ይህንኑ ሥራ በባለቤትነት መሥራት፤ ወይም በተሰማራበት የመልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ዘርፍ አካሄድ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ ማድረግ፣

   ለ. በሥራው ሂደት በሚያጋጥመው ኪሳራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የካፒታል መጠኑን መቀነስ፣

   ሐ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራ እንዲያከናውንበት የተሰጠውን የንግድ ስም መቀየር፣

2. ማንኛውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ ያስመዘገበው ታሪፍ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ በታሪፉ ከተመለከተው በላይ ክፍያ መጠየቅ፣
3. በአንድ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ኩባንያ/ድርጅት ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው በሌላ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ኩባንያ/ድርጅት ቦርድ አባልነት መሳተፍ አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት፤ ዕገዳና መሰረዝ

### 11. የሥራ ፈቃድ እድሳት

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ቋሚ የሥራ ፈቃዱን ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ እያቀረበ ማሳደስ አለበት፣
2. የሥራ ፈቃድ ለማደስ ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀው የማደሻ ማመላከቻ ቅጽ በመሙላት እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን በማሟላት የፈቃዱ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ማቅረብ አለበት፣
3. የሥራ ፍቃዱን ለማደስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤
4. በዚህ አንቀፅ፣ ን/አንቀፅ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8፣ ን/አንቀፅ 2 መሰረት የተሠጠ ጊዜያዊ የሥራ ፈቃድ አንድ አመት ሲሞላው በቋሚ ፈቃድ መተካት አለበት፣
5. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሥራ ፈቃዱን ለማሳደስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስነውን የማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል፡፡
6. በተጠቀሰው የማደሻ ወቅት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የሥራ ፈቃዱን ያላደሰ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በአንድ ወር ውስጥ ለማሳደስ ካመለከተ ብቻ በገንዘብ ቅጣት ያሳድሳል፡፡

DRAFT

12· <u>*የሥራ ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ*</u>

1. የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ በባለሥልጣኑ ውሳኔ የሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እገዳው ወይም ሥረዛዉ ከመወሰኑ ከሶስት ወራት በፊት በባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የሥራ ፈቃድን ሊያግድ ይችላል፡-

    ሀ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 6 መሰረት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ፈቃዱን ያላሳደሰ ከሆነ፤

    ለ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ታሪፉን በተገቢው ጊዜ ለባለሥልጣኑ አሳውቆ ያላስመዘገበ ከሆነ፤

    ሐ. በአመታዊ ወይም በድንገት በሚደረግ ፍተሻ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱትን ሳያሟላ ሲገኝ፤

    መ. የሥራ ፈቃድ የተሰጠው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የመልቲሞዳል ትራንስፖርትን ሥራን ለመሥራት በዚህ መመርያና አከናዋኙ በገባው ውል መሰረት ብቁ ሆኖ ሣይገኝ የቀረ እንደሆነ፣

    ሠ. ፈቃዱ የታገደበት አከናዋኝ ፍቃዱ ከታገደበት ቀን ጀምሮ የመልቲሞዳል አገልግሎት ለመስጠት አዲስ ውል ሳይገባ ቀድሞ ውል የያዘባቸውን ሥራዎች ብቻ ያከናውናል፤

    ረ. ፈቃዱ የታገደበት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ከባለሥልጣኑ የሚሰጡትን አስተያየቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አሟልቶ ሲገኝና ባለሥልጣኑ የሚወስነውን ቅጣት ከፍሎ ፍቃዱ ይታደሳል ወይም እገዳው ይነሳለታል፤

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የሥራ ፈቃድ ሊሠርዝ ይችላል፡-

DRAFT

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) መሰረት የታገደበትን የስራ ፍቃድ በአንድ ወር ውስጥ ሳያሳድስ ከቆየ

ለ. የሥራ ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም በማጭበርበር ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ እንደሆነ፣

ሐ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በማንኛውም ዓይነት የማጭበርበር ድርጊት ወይም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት ሥራን አስመልክቶ አዋጁንና ይህን መመሪያ የሚጻረር ጥፋት ወይም የወንጀል ድርጊት መሥራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

መ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርትን ሥራ ለመሥራት በአንቀጽ 6 እና 7 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማጓደሉ ምክንያት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት በወቅቱ ማስተካከል ካልቻለ፣

ሠ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሥራ ፈቃዱ በታገደበት ወቅት ቀድሞ ውል ከገባባቸው ውጭ አገልግሎት መስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ረ. ባለሥልጣኑ ያወጣውን የሥራ አፈፃፀም ስታንዳርድ (በተለይም የዕቃዎች የባህር ወደብ ቆይታ ጊዜ፣ የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራት ደረጃና የዕቃዎች አያያዝና ደህንነት አጠባበቅ) እንዲሁም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የስነምግባር ደንብን በተደጋጋሚ ማጓደሉ ሲረጋገጥ፤

ሰ. በአንቀፅ 12፣ ን/አንቀፅ 2 መሰረት ለተላለፈበት እገዳ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን ባለሥልጣኑ በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተካክሎ እገዳውን ያላስነሳ መሆኑ ሲታወቅ፣

ሸ. የሥራ ፈቃድ የተሰረዘበት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገና ሊያመለክትና እንዳስፈላጊነቱ ታይቶ ሊፈቀድለት ይችላል፣

13. የሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለመመለስ

የሥራ ፈቃዱ እንዲሰርዝ የተወሰነበት ወይም የሥራ ፈቃዱን ለመመለስ የፈለገ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በባለሥልጣኑ ከሚዘጋጅ ቅጽ ጋር የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፤-

DRAFT

1. የሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለመመለስ የሚፈልግ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ከሶስት ወራት በፊት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማመልከት አለበት፤
2. የሥራ ፈቃዱን ለመመለስ ጥያቄ ያቀረበ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ውል የያዘባቸው ሥራዎችን በሁለት ወራት አጓጉዞ ማስረከብ አለበት፣ አዲስ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት የማከናወን ሥራ አይጀምርም፣
3. በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በእጁ ያለውን የደንበኞች ዕቃ አጓጉዞ ማስረከብ ካልቻለ ግን ደንበኛው ለመረጠው ሌላ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራውን ያስተላልፋል፣ ከደንበኛው የወሰደው አገልግሎት ያልሰጠበት ክፍያ ካለ ታስቦ ተመላሽ ያደርጋል፣
4. መንግሥት ከሚፈልግበት ማንኛውም የግብር ግዴታና ሌሎች ግዴታዎች ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
5. የወሰደውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ፍቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ መመለስ አለበት፣

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14· የባለሥልጣኑ ሰልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ ለባለሥልጣኑ የተሠጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለሥልጣኑ፡

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የሥራ ፈቃድ የተሠጣቸዉን ወይም የሥራ ፈቃዳቸው የታገደውን ወይም የተሠረዘውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ዝርዝር የያዘ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ወቅታዊ መረጃ አዘጋጅቶ ያወጣል፣
2. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች በየጊዜው ሥራ ላይ የሚያውሉትን ታሪፍ በባለሥልጣኑ ማስመዝገባቸዉን ያረጋግጣል፣
3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች የሚጠቀሙባቸዉ ሰነዶች ተስማሚና የአዘገጃጀት ሂደታቸውም ቀላልና ቀልጣፋ እንዲሆን ከሚመለከታቸዉ የባህር በር

DRAFT

ካላቸው ጐረቤት አገሮች ጋር በመመካከርና በማዘጋጀት የሀገራችን የውጪ ንግድ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ያደርጋል፣

4. የመልቲሞዳል ትራነስፖርት አከናዋኞች የሚያቀርቡትና ባለስልጣኑ ያጸደቀውን ታሪፍ በሚስጥር ይይዛል፤
5. የመልቲሞዳል አገልግሎት ስታንዳርድን፣ የአሰራር ሥርዓት፣ የመልቲሞዳል አከናዋኝ ስነምግባር ደንብን ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ መዋሉን፣ ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤
6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ን/አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበውን ታሪፍ ከወቅታዊ የዓለም አቀፍ የዘርፉ ገበያ፤ ከሀገሪቱ የዋጋ ግሽፈት፤ ከውጭ ምንዛሬ ግብይት እና ሌሎችም መመዘኛዎች መሰረት በማድረግ የታሪፉን አግባብነት መርምሮ ያጸድቃል፤
7. የጸደቀውን ታሪፍ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለመልቲሞዳል አከናዋኙ በጽሁፍ ያሳውቃል፣
8. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ን/አንቀጽ 12 መሠረት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ጊዚያዊ የሥራ ፈቀድ በሰጠ ከ3 ወራት በኂላ በ5 ቀናት ውስጥ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በሚያቀርብለት ጥያቄ መሰረት በዝግ አካውንት የተቀመጠው ገንዘብ እንዲለቀቅ ለባንኩ በደብዳቤ ያሳውቃል።
9. የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 እና 13 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣
10. የአዋጁና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ባግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶ ስራ ላይ ያውላል።

15· <u>የብሔራዊ ባንክ ስልጣንና ተግባር</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተደነገገውን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ አጠቃቀም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

2. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች የሚያስፈልጋቸውን የውጭ ምንዛሬ በተመለከተ ባንኩ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር እና አፈጻጸሙን የሚከታተልበት ስርዓት ያዘጋጃል፡፡

## 16. <u>የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር</u>

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ዕቃዎች በመጓጓዝ ላይ እያሉ በመጥፋት ወይም በመሰረቅ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጽና ታክስ መሸፈኛ የሚውል አስፈላጊውን የጉምሩክ ዋስትና (Customs Bond) በማሟላት ከባህር ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ መዳረሻ እንዲያጓጉዙ ያመቻቻል፤ ይከታተላል፡፡

## 17· <u>በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ</u>

1. የንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ወይም የንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው በኂላ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የተሰረዘበት ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት አመልካቹ ወይም አከናዋኝ በውሳኔው ቅር ከተሰኘ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 (2) መሠረት ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በተሰጡ በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብን ቅሬታ መርምሮ ለሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ ለሚወከል የሥራ ኃላፊ የውሳኔ ሃሣብ የሚያቀርብ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ያቋቁማል፡፡ ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ያደረጋል፤
3. ማንኛውም ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ቅሬታው ተመርምሮ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ውሳኔው ተፈፃሚ አይሆንም፤ ሆኖም ግን የውሳኔው አለመፈጸም በህዝብ ወይም በመንግሥት ላይ ሊመለስ የማይችል ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ በሚኒስትሩ ውሳኔ ተግባራዊ እንዲደረግ ሊወሰን ይችላል፣

4. የቅሬታ ማስተናገጃ አካሉ የቀረበውን ቅሬታ መረምሮ የውሳኔ ሃሣብ ለሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ ለወከለው የሥራ ኃላፊ ያቀርባል፣
5. ሚኒስትሩ ወይም ወኪሉ በቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል ይህ ውሳኔ የሚኒስቴሩ የመጨረሻ ወሳኔ ይሆናል፣
6. በሚኒስትሩ ወይም በወከለው የሥራ ኃላፊ የተወሰነውን ውሳኔ ወዲያውኑ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፣

DRAFT

7. በሚኒስቴሩ በተሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያሰው ሰው ውሳኔው እንዲከለስ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መሠረት የክለሳ ጥያቄውን ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

18· <u>የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነትና የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2010 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ሕጐች በዚህ መመሪያ ላይ እንደአግባቡ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡
2. ይህን መመሪያ የሚቃረን መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ ለተሸፈኑት ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም፡፡
3. በአሁኑ ጊዜ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎትን እየተገበሩ የሚገኙ አከናዋኞች ይህ መመሪያ በወጣ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ቋሚ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው መሰረት ፍቃድ ካልወሰደ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተጨማሪ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ፍቃድ መውሰድ አለበት፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቋሚ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ ካልወሰደ ሥራ መቀጠል አይችልም፣

19· <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስቴሩ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

DRAFT